አፍሪካ ቲቪ

4

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

በቴሌግራም 6

AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

# ሴት ልጅ በኢስላም

- እምነትንና መልካም ስራን መሠረት አድርጎ አላህ ዘንድ በሚገኝ ምንዳና ትሩፋት ሴት ልጅ ከወንድ ጋር እኩል ናት። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ሴቶች የወንዶች ክፋዮች ናቸው።›› ብለዋል።
- መብቷን መጠየቅ የደረሰባትን ግፍ መከላከል መብቷ ነው። ኢስላማዊ አስተምህሮቶች በግልፅ ወንድና ሴት የሚለያዩባቸውን ጥቅት ጉዳዮች ላይ ካልሆነ በስተቀር ሌላው ነገሮች በሁሉም እኩል ናቸው። ሸሪዓ የፆታ ልዩነቶችንና ተስማሚነትን ይጠብቃል።
 አላህ በቁርአን ‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀት ረቂቁ ውስጥ ዐዋቂው ሲሆን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን?›› ብሏል።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- ኢስላም ለሴቶች የመውረስ መብቷንም ጠብቆላት ተገቢውን ውርስ ሊወርሱ እንደሚገባ በቁራአን በሰፊው ተብራርቷል፡፡
- ሴቶች ወንዶች ሲያገቧቸው መህር (የአክብሮት ስጦታ) ለሴት መስጠት አለበት፤
  - (وَءَاتُواْ ٱلنِّسَآءَ صَدُقَٰتِهِنَّ نِحۡلَةٗۚ فَإِن طِبۡنَ لَكُمۡ عَن شَيۡءٖ مِّنۡهُ نَفۡسٗا فَكُلُوهُ هَنِيٓـٔٗا مَّرِيٓـٔٗا)

•(ሴቶችንም መህሮቻቸውን በደስታ ስጡ፡፡ ለእናንተም ከእርሱ አንዳችን ነገር ነፍሶቻቸው ቢለግሱ መልካም ምስጉን ሲኾን ብሉት፡፡)

•ኢስላም ሴትን በባሏ ቤትም ስልጣን እና አስተዳዳሪ አድርጓታል፡፡

•ሴት ልጅ ለራሷ አፈጣጠር ጋር ተስማሚ የሆነ ስራ ያላት ሲሆን ወንድም እንዲሁም የራሱ የሆነ ስራ አለው፡፡ አንዱ በሌላው ተግባር ጣልቃ መግባት በሕይወት ሚዛን ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ ሴት ልጅ በቤቷ ቁጭ ብላ ወንድ በየቦታው ለፍቶ የሚያገኘውን ያህል ታገኛለች፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- ከሸሪኣው ጋር በማይጋጭ መልኩ ሐላል ሐራሙን ተረድታ መሰረታዊ የዲኗ እንቅስቃሴ ላይ ተፅኖ በማያሳድርግባት መልኩ ሸሪዓን ጠብቃ ራሷን ለማስተዳደር ከቤት ወጥታ የመስራት መብቷንም ጠብቆላታል፡፡ መስራት ሲያስፈልጋት እና ሁኔታው ሲያስገድዳት መሆንም አለበት፡፡
- ከቤት በመውጣትም የተለያዩ መስጂዶች እና መርከዞች ትምህርት ቤት በመሄድ ዲናዊ እውቀቷን መቅሰም ይፈቀድላታል፤ ይህም ሸሪዓውን ለመረዳት፤ ሐላል፤ ሐራሙን መረዳት፤ ቁርዓንን መማር እና ሐዲሶችን መማር እና የመሳሰሉት፡፡

4

አፍሪካ አካዳሚ

- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በይሀቂ በዘገቡት ሐዲስ አስማእ ቢንት የዚድ የተባለች ሴት ነብዩ (ﷺ) ከሱሃቦቻቸው መካከል ባሉበት መጥታ እኔ ወደ እርስዎ የተላኩ የሴቶች መልዕክተኛ ነኝ በምስራቅ ትሁን በምዕራብ የእኔን ተልዕኮ ትስማም አትሰማ ሁሉም ሴቶች በዚሁ ሀሳብ ላይ ይስማሙበታል፡ ይኸው አላህ ለወንዶችም ለሴቶቹም በትክክል ልከዎታል እናም በእርስዎም በላከዎት ጌታም በአላህ አምነናል፡፡ እኛ ሴቶች በቤት ውስጥ የተገደብንና የተወሰነን የቤቶቻችሁ ጠባቂዎች የስሜታችሁ መውጫዎች የልጆቻችሁ ተሸካሚዎች ነን፡፡ እናንተ ወንዶች ግን ከእኛ በተለየ በጁምዓና በጀመዓ በሺተኞችን በመጎብኘት የሞተን በመቅበር በየጊዜው ሐጅ በማድረግ ታድላችኋል፡፡ ከዚህ ሁሉ የሚበልጠው ደግሞ ለአላህ ሲባል እስከ ሕይወት መስዋዕት ለመክፈል ተመርጣችኋል፡፡ ወንዶች ለሐጅ ወይም ለዑምራ ለጅሃድ ስትወጡ ንብረታችሁን እንጠብቃለን ልብሶቻችሁን እንፈትላለን ልጆቻችሁን እናሳድጋለን እና በምንዳው አንጋራችሁ ምን አለች በዚህ ነብዩ ወደ ሶሃቦች መለስ ብለው ስለ ዲኗ የጠየቀች ሴት ከዚህች ሴት የበለጠች ብለን አስበን አናውቅም አሉ፡፡ ከዚያም ነብዩ ወደ እሷ ዘወር ብለው ‹‹ተመለሺ የላኩሽን ሴቶች ማንኛውም ሴት ለባሏ ጥሩ ሚስት መሆኗ የእሱን ደስታ ማሰቧ ፈቃዱን መከተሏ ይህን ሁሉ ይመዝናል ብለሽ አስተምሪ ሲሏት ላኢላሀኢለሏህ አላሁ አክበር እያለች በደስታ ተመለሰች››



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በይሀቂ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ውስን ሴቶች ወደ ነብዩ መጥተው ወንዶች ከእኛ በጂሃድ በለጡን እነሱን የምንደርስበት ሌላ ስራ የለንም ወይ በማለት ጠይቀዋቸዋል ሴት ልጅ የቤት ስራዋን በመስራቷ ብቻ የሙጃሂዶችን አጅር ያሰጣታል›› ብለዋል፡፡
- ከዚህም አልፎ ለሴት ዘመድ በጎ መዋል ከፍተኛ ተግባር እንደሆነ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድና ጦቦራኒ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ሁለት ሴት ልጆች ወይም ለሁለት እህቶች ወይም ለሁለት ዝምድና ባለቤት ሴቶች አላህ እስከሚያበቃቃችው ድረስ በአላህ ብሎ የረዳቸው ሰው ከጀሀነም እሳት መከላከያ ይሆኑለታል›› ብለዋል፡፡

አፍሪካ አካዳሚ

- የፊትን እና የቅንድብን ፀጉር መንጨት ክልክል ሐራም ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ቀነዳቢን እና ተቀንዳቢን የአላህ እርግማን ይውረድባቸው›› ብለዋል፡፡
- ሴት በጣም ችግር ካልገጠማት በስተቀር የራስ ፀጉሯን መላጨት ክልክል ነው፡፡ ሁኔታው ካስገደደ ግን ከወንድ ጋር በማያመሳስል መጠን ማሳጠር ትችላለች፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹በወንድ የሚመሳሰሉትን ሴቶች ነቢዩ ረግመዋቸዋል›› ወይም ከካፈር ሴቶች በማያስመስላት መልኩ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ‹‹ከሰዎች ጋር የተመሳሰለ ሰው ከእነሱ ነው፡፡ ብለዋል፡፡
- የራሷ ተፈጥሮ ጸጉር ላይ ሌላን ፀጉር መቀጠልም ክልክል ሐራም ነው፡፡ የሌላ ሴት ፀጉርም ሆነ የእንስሳ ፀጉር በፀጉሯ ላይ መቀጠል ክልክል ነው፡፡ ከአካላቷ መካከል አንዱንም መነቀስ ክልክል ነው፡፡ ሁለቱም ተግባሮች ከታላላቅ ወንጀሎች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ነብዩ ቡኻሪና ሙስም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ቀጣዩም አስቀጣዩም ነቀሿም ተነቃሿም
 የአላህ እርግማን ይውረድባቸው›› ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com